# የጎሳ ፖለቲካ የፍፃሜው ዋዜማ

አገራችን ኢትዮጵያ የተማሪዎችን እንቅስቃሴ ተከትሎ የብሔር ፖለቲካ ሲራገብ እና መሰረቱንም እየሳተ ለዘመናት ተከባበረው የኖሩ ሕዝቦችን ለማጋጨት እናም በመሃከላቸው መተማመን እንዳይኖር ለማድረግ የራሱን አስትዋጽኦ እንዲያበረክት በተለያዩ ወገኖች ሲሰበክ የኖረ ጉዳይ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው ። ሰሞኑን የአቶ ስየ አብርሃ እና የዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲን መቀላቀላቸው ሲሰበክ የኖረወን በዘር ላይ የተመሰረተን ፖለቲካ የማብቂያው መጀመሪያ በመሆኑ ከከፍተኛ አክብሮት ጋር እንክዋን ወደ አንድነቱ ሃይል ተቀላቀላችሁ ስል ያለኝን አድናቆት እና አክብሮት ልገልጽ እወዳለሁ ።

የሁለቱ ግለሰቦች ወደ አንድነቱ ጎራ መቀላቀል ለትግሉ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን አስተዋጻኦዎች ያበረክታል ብየም አምናልሁ ::

1. ወያኔ / ኢህአዴግ ከአሁን በፊት ጠንከር ያለ ድርጅት ሲገጥመው ነፍጥኞች የቀድሞ ስርአት ናፋቂዎች ወዘተ.በማለት ከፍተኛ የሆነ የማጥላላት ዘመቻ ሲያካሂድ እንደኖረ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል ። በቅንጅት ለደሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲም ላይ የተፈፀመው ግፍ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው ። ስለዚህም የስርዓቱን የፕሮፓጋንዳ ማሽን በአንድነት ፓርቲ ላይ እንዳይደግመው አፉን የሚያዘጋ እርምጃ ነው ።

2. አቶ ስየም ሆኑ ዶክተር ነጋሶ የወያኔ / ኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ስለነበሩ የስርዓቱን ደካማም ሆነ ጠንካራ ጎን ጠንቅቀው ያውቃሉ ከፍተኛ የስራ ልምድም ሆነ ተሞክሮ ያላቸው በመሆኑም ለትግሉ የሚጠቅም አስትዋጽኦ ያበረክታሉ ።

3. ወደፊት በኢትዮጵያ ውስጥ በዘር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ እያበቃለት እንደሆነ ያበሰረ እርምጃ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ የሆነ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት እጦት ችግርን በጋራ በመቆም መታገል ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን ለማስተማር እናም ወደፊት ልንገነባት ለምንፈልጋት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋን የሚፈነጥቅ ስራ ለመስራት የግለሰቦቹ ድርሻ ከፍተኛ ነው ። ወያኔ / ኢህአዴጎችም እንደተለመደው አንድን ብሔር ከሌላኛው ጋር እያጋጩ የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም የሚሰሩተን ተንኮል በመስበር ትግሉን ያግዛል ።

4. . የአቶ ስየም ሆነ የዶክተር ነጋሶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር እዛው አገር ውስጥ ከሕዝቡ ጎን በመሆን ለመታገል መቁረጣቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ስለሚሆን ሕዝቡም ታገሎ ሊያታግለው የቆረጠን እናም የፖለቲካም ሆነ የልምድ ብቃት ያላቸውን ከጎኑ ሲያገኝ ስለሚበረታታ ያለው ጥቅም ለማንም በንፁህ አእምሮ ለሚያስብ ሰው ግልፅ ነው ።

5. የሁለቱም ግለሰቦች ውሳኔ ሌሎችን ከስርዓቱ ጋር የሚሰሩትን ኀይሎች የሚያበረታታ በመሆኑ የነሱን ፈለግ በመከተል የሕዘቡ አጋር እንዲሆኑ ይጋበዛል በሂደተም ሰርዓቱ ባዶውን እንዲቀር እናም እንዲጠፋ ሊያደርግ ይችላል ለዚህም የኛ አቀባበል ወሳኝንት ይኖረዋል ።

ከላይ ይህን ያህል ባጭሩ ስለሚኖረው ጥቅም ከገለፅኩኝ እኔን በጣም የገረመኝና ያሳዘነኝ ጉዳይ ላይ ትንሽ ለማለት እወዳለሁ የግለሰቦቹ የአንደነት ፓርቲን መቀላቀል የሚያበስረወን ዜና ተከትሎ በአንዳንድ ሚዲያዎች አካባቢ በተለይም የአንድነት ፓርቲ ደጋፊ ነን ከሚሉ ወገኖች በተቃውሞ የሚሰነዘረው አስተያየት ትግሉን በምንም ቀመር የማይጥቅመው ሆኖ አግኝቼዋልሁ። ምክንያቱም ሁለቱም ግለሰቦች ስርዓቱን ጥለው የአንድነቱን ኀይል በመቀላቀል ለመታገል ሲወስኑ የመጀመሪያ ሰዎች አይደሉም ። ከነሱ በፊትም ብዙዎች አገዛዙን ጥለው በመውጣት ለአገዛዙ መለወጥ የራሳቸውን ደርሻ እያበረከቱ ይገኛሉ የተወሰኑትም በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በአመራርነት እያገለገሉ ይገኛሉ ወደፊትም የአገዛዙን ጎራ እየጣለ ለመታገል የሚወስንን ማንኛውንም ግለሰብ እጃችንን ዘርግተን መቀበሉ እናም የጠላትን ጎራ ማዳከሙ የግድ ይላል ። ከዚህ በተረፈ ለምን ወደ ሕዝብ ጎራ ተቀላቀላችሁ እዛው ከአገዛዙ ጋር በመቀጠል የኢትዮጵያን ሕዝብ ስቃይ አራዝሙት ብሎ አስተያየት መስጥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከማሰብ በጭራሽ ሊሆን አይችልም ። አንዳንዴም ከጠላት መማር ያስፈልጋል ውያኔ / ኢህአዴግ እኛን ለመበታተን ከመሃላችን ስንቱን ሲማርክ አይተናል ።

አንዳንዶች እንደሚሉት እነዚህ ግለሰቦች የአንደነቱን ጎራ የተቀላቀሉት ስልጣን ፍለጋ እንደሆነ ሲገልጹም ይደመጣሉ ይህን አባባል እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ምንም መሰረት አይኖረውም ግለሰቦቹ ስልጣን ቢፈልጉ ሌሎች እንዳደርጉት ከአገዛዙ ጋር በመሰማማት የፈለጉትን ማግኘትና ቀድሞ ወደ ነበሩበት ወንበር ላይ ለመመለሰም አጭሩና ቀላሉ መንገድ ይሄው ብቻ ይሆን ነበር ። አቶ ስየም ሆኑ ዶክተር ነጋሶ በተደጋጋሚ ሔደውበት የነበረው ጎዳና የተሳሳተ እንደነበር አሳመረው ገልጸዋል ። ከስህተታቸው በመማርም ለአሁኑ ውሳኔ ደርሰዋል :: ከስርአቱ ጋር እየሰሩ ባሉበት ወቅት ለተፈጸሙ ስህተቶች ተጠያቂ እንደሆኑ በመግለፅ በተለያየ አጋጣሚ ይቅርታ ሲጠይቁ ተደምጠዋል በመሆኑም የይቅርታ

ደብዳቤ ለእያንዳንዳችን በፖስታ ይላኩልን የምንል ካልሆነ በስተቀር በውሳኔያቸው ልንኮራባቸውና ለናበረታታችው ይገባል ። ማበረታታቱ ቢከብደን እንክዋን ዝም ማለቱ ይሻላል እንጂ እከሌ ወንጀለኛ ነው ብለን ከሰን እራሳችን ስንፈርድ አለማስተዋላችንን ያሳያል ። አገዛዙም እያደረገ ያለው ይሔንኑ ነው ። እከሌ ወንጀለኛ ነው ብሎ በነጻ እና ገለልተኛ ፍርድ ቤት ሳይታይለት ያስራል እንደፈለገ ያደርጋል ። እኛም ይሄን አካሄድ እየታገለን እያለን መልሰን ግን እኛው እናደርገዋለን ልዩነቱ እኛ እንደ አገዛዙ የማደርግ አቅሙ ስለሌለን ወይም ስልጣን ላይ ስላልሆነን ነው ። በኢትዮጵያችን ነጻና ገለልተኛ ተቁዋማት ሲኖሩን ወይም ደሞክራሲያዊ ስርዓትን የገነባን ጊዜ በኢትዮጵያና ሕዝቦችዋ ላይ ወንጀል የሰራ በሙሉ ይጠየቃል ። ይህንን ለአገራችን የምንመኘውን ስርዓት ሳንገነባ ከወዲሁ እርስ በእርስ መወነጃጀሉ የሚጠቅመው አገዛዙን ብቻ ነው ። በኔ እምነት ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ወዲህ እንክዋን ብቻ በተለያዩ ወገኖች ብዙ ወንጀሎች ተሰርተዋል ስለዚህ በአሁኑ ወቅት መካሰሱንም ሆነ መወነጃጀሉን ወደ ጎን አድርገን ይልቁንም አይናችንን በአሁኑ ሠዓት መሳሪያና ጉልበቱን ተማምኖ ሕዝባችንን የመከራ ሒወት እንዲገፋ እያደረገ ባለው ወያኔ / ኢህአዴግ ላይ መትከሉ የሕዝባችንን ችግር እና መከራ የሚያሳጥረው ትክክለኛ መንገድ በመሆኑ ልንጠነቀቅ ይገባል ።

ከሻዕቢያ ጋር መስራት ይቻላል የኦረሞ ነፃነት ግንባር ወይም የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር የትግል አጋር መሆን ይችላሉ ብለው ከሚያምኑ ወገኖች በሌላ በኩል ደግሞ የጥላቻ ፖለቲካ ጊዜው ያለፈበት ነው ከአገዛዙ ጋር በመነጋገር በጋራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መገንባት ይቻላል ብልው ከሚያስቡ ወገኖችስ በምን ሎጂክ ይሆን የእነ አቶ ስየ አበርሃ አንደነትን መቀላቀል የሚረበሻቸው ? በአንድ በኩል ፀረ ኢትዮጵያ ከሆኑ ሃይሎች ጋር መሰራት ይቻላል በሌላ በኩል ደሞ አይቻልም ( ያውም ከስህተታቸው ተምልሰው የሕዝብ ወገንተኛነታቸውን ለማሳየት ከሚሰሩ ግለሰቦች ጋር ) እያሉ አስተያየት መስጠት አንድም የምናደርገውን ካለማውቅ አልያም የተደበቀ አላማ ሲኖረን ብቻ ነው ። ከነ አቶ አረጋዊ በርሄ ጋር የሰሩ እስከ አሁንም እየሰሩ እናም አገዛዙን እየታገሉ ያሉ ወገኖቻችንስ የነ አቶ ሰየ አንድነትን መቀላቀል ይረብሻቸው ይሆን ?መልሱ አይሆንም ነው። ከኢህአፓ እና ሚኤሶንም በጋራ ሆነው ወያኔ / ኢህአዴግን መታገለም የምንማረው ይሄንኑ ነው ወደ ሁዋላ ተመልሰን እንወነጃጅል ቢባል የት ሊደረስ ማንስ ሊጠቀም ? ባጠቃላይ የሁለቱ ግለሰቦች ወደ ሕዝብ ጎራ መቀላቀል እና አገዛዙን መታገል ማንንም ኢትዮጵያዊ የሚረብሽ ሊሆን አይችለም ። በተቃራኒው የግለሰቦቹ ውሳኔ ወያኔ /ኢህአዴግንም ሆነ ሌሎች ፀረ ኢትዮጵያ ሃይሎችን እንደረበሻቸው ብዙ ምልክቶች እየታዩ ነው በምሳሌነት አይጋ ፎረምን መጥቀሱ ይበቃል

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ሳዓት የሚያውቀው ግለሰቦቹ አገዛዙን እየታገሉ መሆናቸውን እና እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የስርዓቱ ተጎጂዎች መሆናቸውንም

ጭምር ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ቀድሞ በሰሩት ሳይሆን አገዛዙን ከጎኑ ሆነው እየታገሉ ስላሳዩት በተለያዩ አጋጣሚዎችህ ለግለሰቦቹ ያለውን አክበሮት ሲገልፅ ታይትዋል በምሳሌነትም የአንድነት ፓርቲ በጠራው የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ሲጋበዙ እናም ወደ መድረኩ ሲወጡ የነበረውን ጭብጨባና ደጋፍ የምናስታውሰው ነው ቪዲዮውን እዚህ ላይ በመጫን መመልከት ይቻላል

http://video.google.com/videosearch?q=andent+public+meeting&emb=0&aq=f#q=andinet_final_part_two&view=2&emb=0&qvid=andinet_final_part_two&vid=-7402045341287393360 ታድያ እኛ በውጪ አገር የምንኖር እትዮጵያውያን በምን ሒሳብ ነው አገር ቤት ያልውን ወገናችንን እናውቅልሃለን የምንለው ? በመሃላችን እርግጥ ነው ሰርገው የገቡ የአገዛዙ ጉዳይ አስፈጻሚዎች እናም የኢትዮጵያን መጥፋት የሚመኙ ሃይሎች እንዳሉ የታወቀ ጉዳይ ነው ። ሳጠቃልልም ወያኔን መታገሉ እንዳለ ሆኖ የሌሎች መጠቀሚያ እንዳንሆን እንጠንቀቅ ድጋፋችንንም በአግባቡ እንደምናምንበት ድርጅት እናድርግ የኢትዮጵያ አምላክም አገራችንን ከጥፋት ይጠብቅ አሜን ።

ብርትኳን ትፈታ !!!

ዜግነት ከምድረ ኦስትሪያ